የ፳፻፪ ትክክለኛ ምርጫ ልሣን
ምርጫው በጎዥው ክፍል ተዘጋጅቷል።
ሕዝቡ ያለውዴታው ይሣተፋል።
የእኛም አስተዋፅዖ እነሆ።

# እስከመቼ

የካቲት ፳፰ እስከ መጋቢት ፬ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.
March 7 to March 13, 2010
ቅፅ ፩ ቁጥር ፰
Volume I Number 8

## ሦስተኛ መሥመር ወደፊት ወደኋላ መደናበር

በኢትዮጵያ የአሁን የፖለቲካ ሃቅ፤ ሁለት ሠፈሮች ብቻ ነው ያሉት። እያንዳንዱ ሠፈር የሚያራምደው የራሱ የሆነ የአመለካከት መሥመር አለው። ለሕዝቡ፤ የሕዝቡ መሥመር አለያም የኢሕአዴግ መሥመር ብቻ ነው ያለው። ለኢሕአዴግ ደግሞ፤ የኢሕአዴግ ወይንም የኢሕአዴግ ጠላቶች መሥመር ብቻ ነው ያለው። ታዲያ ምን አዲስ ነገር ተፈጥሮ ነው ሦስተኛ መሥመር የተከሠተው? በዛሬዋ የ**እስከመቼ** ቁጥር ፰ ይኼን ክስተት እንዳስሳለን።

የተያዘው የምርጫ ሽርጉድ የትግሉ አካል ነው። ስለሆነም በዚህ ዙሪያ የሚንፀባረቁት በኢሕአዴግ የግዛት ዘመን ያለውን አንድ ጠቅላላ ሃቅ ነው። ይህ ሃቅ በምንም ዓይነት ቀለም ተቀባ በምን ምንነቱ አይቀየርም። በፖለቲካው ግብግብ ሁለት መሥመር ብቻ መኖራቸው!

ሕዝቡ ለኢሕአዴግ፤ ኢትዮጵያዊ ትዕግሥቱን እስከ እንጥፍጣፊው አሟጠ፣ ይቅር ባይነቱን እስከ መጨረሻው ለግሶ፣ ያለ የሌለውን ገብሮ፤ አይቶታል። እናም በቃኝ አለ። መሥመሩን ከኢሕአዴግ ለየ። በዚህ ሌላ አማራጭ የለውም። ከተደረደሩ የፖለቲካ መሥመሮች የሚመርጥበት ቅንጦት የለውም። በአሁን ሰዓት ካለበት ማነቆ ወጥቶ ለዚህ ቅንጦት ለመብቃት የራሱን መሥመር አብጅቷል።

በዚህ አንፃር ደግሞ ኢሕአዴግ ተሠልፏል። ኢሕአዴግ ለኢትዮጵያ የሚያውቀውን፣ የሚችለውን፣ እናም የሚፈልገውን ሠርቷል። ከዚህ የተለየ መሥራት፤ ዕውቀቱ፣ ብቃቱና፣ ፍላጎቱ እንደሌለው በግልፅ አስቀምጧል። ስለዚህ፤ በኢሕአዴግ ዓይን፤ ይህ ብቻ ነው ለኢትዮጵያ የሚበጃት። ይህ የጠራ መሥመር ነው። ከዚህ የወጣና ይኼን የማይቀበል የኢሕአዴግ ጠላት ነው። እናም በኢሕአዴግ እምነት የኢትዮጵያ ጠላት ነው። (ኢሕአዴግ ማለት ኢትዮጵያ ማለት ነውና!) ይህ የጠላት ክፍል የሚያቀርበው ምርጫና የሚያራምደው መሥመር፤ የኢሕአዴግ ጠላቶች መሥመር ነው። ለዚህ ዋናው ምክንያት ከኢሕአዴግ መሥመር ውጪ ሌላ መሥመር መኖር ስለሌለበት ነው። አንድ ሃቅ ብቻ ነው ያለው። እሱም የኢሕአዴግ የግል ሀብት ነው። ማንም ሌላ ሃቅ መተንፈስ ቀርቶ ማለም የለበትም። አራት ነጥብ።

<u>ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ!</u> ሁለት የጠሩ መሥመሮች ከፊታችን ተቀምጠዋል። የትኛውን መምረጥ እንዳለብን እያንዳንዳችን የምንወስነው የየግል ድርሻችን ነው። ከዚህ ውጪ ሦስተኛ መሥመር የለም። ሕዝቡን ወደ ኢሕአዴግን ፈርቶ ወደፊት መጓዝ አይቻልም። እንዲያ ያለ መሥመርም መቆሚያ እግር የለውም። ከኢሕአደግ ጥቅምን ከሕዝብ ድጋፍን የሚያስተናግድ መሥመርም ሊፈጠር ቢሞከር የጀርባ አጥንት ያጥረዋል።

<u>ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ!</u> ትክክለኛውን መሥመር እንምረጥ። የሕዝብ መሥመር። **እስከመቼ** በኩራት የወገንችለት። አሁን ካለንበት ወደኋላ ጉዞ ቆም ብለን፤ ፊታችንን ወደስተፊቱ አዙረን ቀናውን እንድንጓዝ የምናደርግበት። የመሸጋገሪያ ዘመን። ከትክክለኛው ምርጫ በፊት ያለ የሀገር አድን ጥሪ። የአንድነት ኃይሎች ስብስብ ኢሕአዴግን ይተካ ዘንድ ቆርጦ መነሣት። የትናንትን አደራና የነገን ታሪካዊ ኃላፊነት ዛሬ መወጣት።

<u>ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ!</u> **እስከመቼ** በራሷ ምርጫ፤ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በኃላፊነት ወስዳለች። ኃላፊነቱ የኔም ነው የምትሉ ካላችሁ፤ ጋባዥ አያስፈልጋችሁም በeske.meche@yahoo.com ተገናኙን።

- የምርጫውን ሂደት በዝርዝር መከታተል
- ለመድረክ ድጋፍ ማሰባሰብ
- ፎቶግራፎችን፣ ስም ዝርዝሮችንና፣ ቦታዎችን ከተጠያቂ የኢሕአዴግ አባል ስም ዝርዝር ጋር ለዓለም የዜና አውታሮች ማሠራጨት

**የእስከመቼ ዕትም የዝግጅት ቦርድ፤**
ድረስ ነጋ፣ ሕሊና ነጋሣና፣ ሀገሬ ተመቼ
eske.meche@yahoo.com